መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት

አቅራቢዎች

# እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠው ተስፋ



ጸሐፊው: Edward Hughes

ምሣሌ አቅራቢው: Byron Unger; Lazarus

ያሻሸለው (አሻሸሎ የጻፈው): M. Maillot; Tammy S.

የተተረጎመው: Abel Eshetu

አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org

©2015 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል
ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።



ከጥፋት ውሀ በኋላ
በምድር ላይ የነበሩ
ሰዎች አንድ ሀሳብ
ነበራቸው።

ተስማምተውም “ጬፉ ወደ ሰማይ
የሚደርስ ግንብ እንስራ” አሉ።
አንድ ላይ በሕብረት እንኑር አሉ።
አንድ አይነት ቋንቋ ይናገሩ፣
በአንድ ላይ ይኖሩም ነበር።





እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ
በምድር ላይ በተለያየ ቦታ
እንዲኖሩ ይፈልግ ነበር።
ስለዚህ አንድ አዲስ ነገር
አደረገ። ሰዎች ሁሉ የተለያየ
ቋንቋ እንዲናገሩ አደረገ።

አንድ አይነት ቋንቋ የሚናገሩት አንድ ላይ መኖር
ጀመሩ። እግዚአብሔርም በዚህ ሁኔታ ሰዎች የተለያዩ አገራትን
እንዲመሰርቱ አደረገ። ትተዋት የሄዱት ከተማ ስም ባቢሎን ሲሆን
ትርጉሙም መደበላለቅ
ማለት ነው።



ከአመታት በኋላ
በከለዳውያን ኡር
ምድር እግዚአብሔር
አብራምን እንዲህ
አለው፡- ይህን ምድር
ትተህ እኔ ወደማሳይህ
ምድር ሂድ። አብራምም
እግዚአብሔርን ታዘዘ።
ወደ ከነዓን ምድር
ወሰደው።



ከእርሱ ጋር ሚስቱ ሳራ እና የወንድሙ ልጅ ሎጥ አብረውት ሄዱ።



በከነዓን ምድር አብራምና ሎጥ ሃብታም
ሆኑ። በርካታ የከብት መንጋ ነበራቸው።
ነገር ግን መንጋቸውን የሚያሰማሩበት
በቂ ቦታ አልነበራቸውም።



የሎጥ እረኞች ከአብራም እረኞች ጋር ተጣሉ። አብራምም ይህ ችግር መሆን የለበትም፤ መለያየት እንችላለን፤ ሎጥ የፈለከውን አገር ውሰድ አለው።



ሎጥም በዮርዳኖስ ዙሪያ ያለውን
አገር ሁሉ መረጠ። ሳር የሞላበት
ነበር። ይሁንና ያ አገር አመጸኞች
የሞሉበት ነበር።





ሎጥ ከሄደ በኋላ እግዚአብሔር ለአብራም እንዲህ አለው፡- የከነዓንን ምድር ለአንተና ለዘርህ እሰጣለሁ። አብራምና ሦራ ልጅ የላቸውም ነበር።



ሶስት ሰዎች ከእግዚአብሔር
ዘንድ ተልከው መጡ።



መጡና ሦራን ወንድ ልጅ ትወልጂያለሽ አሉ። ሳራ ግን ሳቀች። የእግዚአብሔርን ቃል አላመነችም ነበር። ሦራ 99 ዓመቷ ነበር። እግዚአብሔር አብራምን አብርሃም፣ ሦራን ደግሞ ሳራ ብሎ እንደሚጠራቸው ነገራቸው።



እግዚአብሔር ሰዶምና ገሞራን እንደሚያጠፋቸው ለአብርሃም ነገረው። ሎጥ ከቤተሰቡ ጋር በሰዶም ምድር ይኖር ነበር።

ሎጥ የእግዚአብሔርን
ማስጠንቀቂያ ሰማ። የልጆቹ
ባሎች ግን ከሰዶም
መውጣት አልፈለጉም።
በጣም ያሳዝናል!
የእግዚአብሔርን ቃል
አላመኑም ነበር።



ሎጥና ሁለቱ ሴት ልጆቹ
ብቻ አመለጡ። እግዚአብሔርም
በሰዶምና በገሞራ ላይ ከሰማይ
እሳትና ዲን አዘነበ።



የሎጥም ሚስት ወደ
ኋላዋ ተመለከተች፥
የጨው ሐውልትም
ሆነች።



እግዚአብሔር
ለአብርሃምና
ሳራ የሰጠውን
ተስፋ ጠበቀ።
በእርጅናቸውም
ወንድ ልጅ
ወለዱ። ስሙንም
ይስሃቅ አሉት።



አሁን አብርሃም
እግዚአብሔር ለዘሩ
ስለሚሰጠው የከነዓን
ምድር እያሰበ ሊሆን
ይችላል።



ያንን ተስፋ
እግዚአብሔር
አልረሳውም።
እግዚአብሔር ሁልጊዜ
ቃልኪዳኑን ይጠብቃል።



እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠው ተስፋ

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ዘፍጥረት 11-21

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

መጨረሻ

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን
እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል።
የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን
አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት
እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው።
ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ!
ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝነት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል
ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል። እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤
እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት
ለመሞት ስትል ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባ
ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን ይኖረኛል አንድ ቀን
ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና
እንደ ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16